
# “ኤርትራ? ኤርትራ? ኤርትራ ደግሞ ማናት? ኤርትራ ያለቀላት የተበላሸች መንደር!

## ጌታቸው ረዳ (Editor- Ethio  Semay)

**“Eritrea Licks its wounds”** (quoted BBC Focus on Africa - during the Badime war between Eritrea bandits and Ethiopia gallants)








ጌታቸው ረዳ

ከላይ የሚታዩ ፎቶግራፎች፤ ዓለም ያከበራቸው የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ኃይለሥላሴና የዚህ ትችት አዘጋጅ ጌታቸው ረዳ ናቸው።

ሰሞኑን በነፃነት ራዲዮ አዘጋጅ አቶ አለም ፈቃደ እና በባንዳው ንአመን ዘለቀ ለመተቸት አስቤ ያንን በይደር አቆይቼ ይህንን ቀዳሚ አድርጌዋለሁ።የአቶ አለም ፈቃደ ታላቁ አንዳርጋቸው ጽጌ በምን ትአምር “ታላቁ አንዳርጋቸው” ብለው እንደሾሙት ለመጠየቅ የተበላሹ የኢትዮጵያዊያን ተቃዋሚ ሚዲያዎች ባሕሪ በመሆኑ ለምደናቸዋልና ወደ እዚሁ ጽሁፍ ይገኡአችሁ ላምራ።  ይህ ጽሑፍ በሳምንታዊ የትችት አምዴ ከሁለት አመት በፊት በድረ ገጾች ተለጥፎ የነበረ ነው። አስፈላጊ ሆኖ ስላገኘሁት መጠነኛ መሻሻል ተደርጎበት የቀረበ ነው።

ከዚያ በፊት ከአንባቢዎቼ የተላኩልኝን “የቴክስት” መልእክቶች ጥቂቶቹን ላስነብባችሁ። በአንዲት እህት ጽሑፍ ልጀምር። እንዲህ ይላል፤-

"Good Morning our Hero, Gecho!!! I ask God to stand next to you as he stands for his kids. I went to bed with tears and wolk up with tears. You did an excellent job. You expose Shaabiya gangs and Ginbot 7 to our society to what is going on in Eritrea prisons. I can't continue- my eye still burns. Have a bless day. We love you. Keep up the good work. Peace!"

ሌላኛው ደብዳቤ፤ የሚለው፤-

"ወንድሜ ጌታቸው ረዳ፤ እንደምን አለህልኝ። ሁሌም ታስደስተኛለህ። ያንተን ጽሑፍ ሳነብ፤ ሕሊናየ ይበረታል። ምነው እንደ ቀድሞው አሲምባ ድረገጽ ላይ ጽሑፎችህን አላያቸውም እሳ?" ይላል።

ጽሑፎቼ በድረገጻቸው እንዳይለጠፉ የወሰኑት " የኢሕአፓና የወያኔ አርበኞች ዋለልኝ መኮንን እና ማርታ መብራቱን ተችተሃል" ብለው ነው። ብዙዎቹ ፤ ሁሉም በሚያስብል ድምዳሜ፤የኢትዮጵያ የፖለቲካ ድርጅት ደጋፊ ሚዲያዎች፤ መሪዎቻቸውን እንዲተቹ/እንዲወቀሱ/እንዲታረሙ/እንዲነኩ አይፈቅዱም። መላዕክቶቻቸው ስለሆኑ መላእክቶቻቸውን መተቸት በጠላትነት ያስፈርጃል። ሌሎቻችሁም እንዲሁ ላበረታታችሁኝ አመሰግናለሁ። ለማንኛውም፤ ትችቶቼን ለማንበብ Welkait.com እና Ethiopatriots.com ወይንም በራሴው ድረገጽ በ Ethio Semay ወይንም ብዙዎቹ እኔ በማላያቸው ድረገፆች ላይ ፈላልጋችሁ ልታነብቡኝ ትችላላችሁ። አመሰግናለሁ።

ወደ ጽሑፌ ይዣችሁ ልግባ።

ወያኔና ሻዕቢያ በውጭ ሃይላት ተደግፈው በሕገ ወጥ መንገድ መንግሥትነት ተቆጣጥረው አንድ አገር ለሁለት ከፍለው፤ በ1998 ተጠያቂነት በሌለው ጦርነት ውስጥ የ70 ሺሕ ሕዝብ ህይወት አጥፍተው ሲያበቁ፤ሰሞኑን ደግሞ ***ዛራቸው*** ተነስቶባቸው ቁጥሩ ያልታወቀ የሰው ህይወት እንዳጠፉ በጉራ ሲነታረኩ አደምጠናቸዋል።

በሰሞኑ ግጭት የተለያዩ አስተያየቶች/ትችቶች/ቃለ መጠይቆች ተሰንዝረዋል። ጦርነቱ ተጀምሯል፤ ማን ያሸንፍ ይሆን? የሚሉ ሰነፍ ተቺዎች አንብቤአለሁ፤ ጦርነቱን ለማቆም **ባድሜ** ለኤርትራ ያለ ቅድመ ኩነት/ሁኔታ መሰጠት አላበት፤ የሚሉ፤... ወየኔ ነው ጀማሪ፤..... አይደለም ሻዕቢያ ነው ጀማሪ..... እያሉ ንትርክ ውስጥ የሚገቡ በሁለቱ ወረበሎች የደነዘዙ ብስለት ያጡ ጸሐፍትም አንብቤአለሁ። አንዳንዱ ሰላምና የሰው ልጅ ህይወት በከንቱ እንዳይጠፋ በመስጋት ስጋታቸው በመግለጽ ሰላም እንዲመጣ ሁለቱንም የሚማጸኑ፤ ወይንም አንደኛውን ኮንነው ሌላኛውን ሳይኮንኑ ፤ ወይንም ሁለቱንም ወንጀለኞች እያወገዙ እርቅ ማምጣት አለባቸው ብለው የሚወተውቱ ተቺዎች... አንብቤአለሁ። ይህ ሁሉ

ከተጨባጩ ሃቅ የራቀ ስለሆነ፤ መነሻውና ማቆሚያው በቅጡ ካላወቅነው፤ ሰላም ፤ሰላም፤ሰላም ብቻ ስለተመኘን ሰላም ሊመጣ አይችልም።

ሰላም እንዲመጣ ከተፈለገ፤ ኤርትራኖችም ሆኑ ወያኔዎች፤ ሁለቱም ከሥልጣን ተወግደው፤ ኤርትራን የሚረከብ ቡድን "ኢትዮጵያዊነትን" አክብሮ አንድ አገር የሚያደርግ፤ወይንም ያለ ሕግ የተነጠቅነውን የባሕር ወደባችንን በፈቃዱ ለኢትዮጵያ እንዲያስረክብ የሚፈቅድ ቡድን ሲፈጠር ያኔ ወሳኙና የሰላም ምንጩ እና መፍተሄው ይህ ይሆናል።ያ አናደርግም የሚሉ ከሆነ እና የኢሳያስና የሻዕቢያ መንገድ እንከተላለን የሚሉ ከሆነ፤ ጊዜ ይፈጇል እንጂ በመጪው 'የነቃ ትውልድ" ከባንዳነት የጸዳ አንድ አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ወደ ሥልጣን እንዲወጣ ሲደረግ፤ ወይንም የኢትዮጵያ አምላክ በአስገራሚና አስደንጋጭ ተአምራቱ 'ባንዳው' መለስ ዜናዊና 'አበ ነብሱ' የነበሩት አባ ጳውሎስን በተአምር እንዳስወገዳቸው ሁሉ፤ አንድ አገር ወዳድ አርበኛ ኢትዮጵያዊ ወታደር ወይንም ሲቪል ወደ ስልጣን በመውጣት፤ ባንዳዎች የወሰኑት ውሳኔ ሽሮ ከላይ የተቀሰኩትን የሰላም አማራጭ መንገድ አንወስድም ብለው የሚያንገራግሩ ኤርትራ ቡድኖች ከተከሰቱ፤ የናፈቁትን ጦርነት ከፍቶ፤ ዓሰብን ለ30 አመት የተኮናተሩትን ዓረቦችን አንደለመዱት ማራወጥ እና ባሕሮችንን መለስን መቆጣጠር፤ የአሉላ አባ ነጋ ታሪክ መድገም የመጨረሻው አማራጩ የመፍትሔ ሃሳብ ሲፈጸም ብቻ ነው ሰላም እያልን የምንኳትተው ሕልም እውን የሚሆነው።

ካልሆነ ሰላም ስለተፈለገ፤ መነሻውና ምክንያቱ ሳንዳስስ 'ሰላም'በገዛ ፈቃዱ በነዚህ ወረበሎች ጊዜ ሊመጣ አይችልም።ሁለቱም ወረበሎች የሚሰጡት መልስ ለጦርነቱ መነሻ እና ለሰላም ጠንቅ በመሆኑ፤ ያለ ሕግ የተነጠቅነውን የኤርትራ መሬታችንና በባርነት የያዙትን ሕዝባችንን በድርድር ያስረክቡን። ካልሆነ ጦርነቱ መቼም ቢሆን አይቀሬ ነው። የግንቦት 7 ባንዳዎችም ሆኑ የተቀራችሁ አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊን ኢትዮጵያ አገራችን እንዴት እና ለምን እንደተበደለች ምክንያት አለኝ፤ ምክንያቴን አንብቡ።

በዚህ-ጽሑፍ ሻዕቢያ እና ወያኔዎች ለ25 አመት መልስ ያጡበትና ያሳፈራቸው አንድ አጭር እና ግልጽ ጥያቄ እንመለከታለን። ድሮ በልጅነታችን "እንእኒ" (ሲነበብ ይጥበቅ) የሚባል ዘመን ነበር ሲሉ ወላጆቻችን ያጫውቱናል። እኛም ያንኑ ትረካ ተቀብለን 'ዝናብ ሲዘንብ' ጓደኛሞች የሆንን ሁሉ ሁሌም በምንጫወትበት ሞቃታ ስፍራ ሰብሰብ ብለን ተጠጋግተን በብርዱ ላለመጠቃት ተኮማትረን ተቃቅፈን ስለዘመኑ እውነተኛነት በዓይናችን ያየን ይመስል የራሳችንን ቅጥያ ጨማምረን አጣፍጠን ከፊት ለፊታችን የሚታዩ የድንጋይ ኮረቶች ሁሉ የዛው

“For the record, both Mr. Meles and Mr Isaiass, and many others, were sitting and listening at the 1991 (July 1-5), "**Charter**" conference in Addis when the martyred Professor Asrat Weldeyes had said:

I submit that this conference has no authority to decide, to desist or to delete anything in the name of the Ethiopian people. However, one recognizes the prevailing de facto situation in the country, including the cessation of bloody hostilities among brothers as well as the current momentum for peace and democracy. EPRDF and EPLF can use their special close relations to see to it that the spirit of **Ethiopianity** and forgiveness be brought to bear to work urgently **for a lasting peace** between the brotherly and sisterly (Ethiopian-Eritrean) people.

“አትዮጵያዊነት!!!” የዘላቂ ሰላም መፍቻውና ቁልፉ እሱ ብቻ ስለሆነ በዛው መንገድ ተዳኙ ነው ያሉት። ያ ጥሳቻሁ፤ረግጣቻሁ፤ንቃችሁ በመንገዳችሁ ከቀጠላችሁ ግን፤ ዘላቂ ሰላም ሳይሆን ዘላቂ ጦርነት ብቻ ነው የሚከተለው ብለው ነበር። እውን “ኢትዮጵያዊነት” እየተናቀ፤ ባንዳነት እየጎለበተ ከሄደ፤ ሰላም የሚባለው የነ ሻዕቢያ እና ወያኔ እንዲሁም ከጥቂት አመታት በፊት የተፈጠሩብን የግንቦት7 አዲሶቹ ባንዳዎች የሚዋሹት “የሰላም መንገድ”፤ አጭበርባሪዎች የቀየሱት የባንዳዎች መንገድ ስለሆነ ሕዝባችን ለሁለተኛ ጥፋት እንዳትራመድ እነዚህን በጠራ ዓይን እና ሕሊና መርምራቸው። ታሪክ አለን! ታሪካችን ባንዳዎችም ሆኑ የተባባሩት ግሳንግስ መንግስታት ማሕብር ሊጠመዝዙት አንፈቅድም። አገር ወዳድ ወይንም ባንዳ የሚያስብለን ታሪካችን እና መልህቃች በጊዜአዊ አስቸጋሪ ማዕበል ስንለቅ ወይንም አጥብቀን ስነይዝ ነው። ሁለታችን የሚለየን ታሪክ በማጉደፍ እና ታረክ አጥብቆ በመያዝ ነው። የወላጆቻችን አደራ አናስበላም። አርበኞች ነበሩን፤ ታሪክና ታሪካቸው አለን;፡ታሪካችን እና ጭብጨጣችንም እነሆ አንብቡ። ኢትዮጵያ አለቀላት ብለው ከጠላቶች ጋር የሚደባለቁ ከሃዲዎች “ኢትዮጵያ እንዳላለቀች” ዛሬም ነገም አለን! አለን! አለን! እንላቸዋለን።፡ታሪካችን እነሆ። መልካም ንባብ....

ጣሊያኖች ወደ አዲስ አበባ ሲገቡ **Ethiopia E Finita !!!!** (ኢትዮጵያ አለቀላት) የሚል መፈክር የያዙ ትሬንታ ኳትሮዎች አዲስ አበባን ወርረዋት እንደነበር ጆን ስፔንሰር Unity and territorial integrity (የግዛት ውሁድነት) በሚለው መጽሐፉ ጠቅሰው እንደነበር አንድ ፀሓፊ በጦቢያ መጽሄት ላይ ጠቅሰው ነበር። የተጠቀሰው መፈክር፤ ዛሬ ያለምን ጥርጥር ኤርትራ ካለ ኢትዮጵያ መኖር የማትችል በጉራ ብቻ የተነዳች፤ ኗሪዎቿ ወደ ኢትዮጵያና ወደ ሰሓራ የሚሰደዱባት፤ደካማ አውራጃዎችን የያዘች፤ ያለቀላት የተበላሸች መንደር ነች። ሰርጓም ሞትዋም በ25 አመት ውስጥ ተጠናቀቀ። ዕጣ ፈንታዋ “ነፃነት” “የኤርትራ መጠለፍ”ን (ፕሮፌሰር ጌታቸው ሃይሌ አገላለጽ) ብላ የገለጸቿውን ነፃነቷን እንደገና “መከለስ” አለባት (ከአመዳም ሕይወት ለመውጣት ስትል!)።ለ25 አመት የተሰጣት “የኦክሲጅን ስሊንደር” አልቋል! ከዚያ ወዲያ መቀጠል full of difficulties/ ነው። ብልሽት!

ነች በለውናል። በኮሎኒያሊስት ካርታ/ማፕ እንዳኛለን ካሉ እኛ የሰጠናቸውን የመጨረሻዎቹ ቅኝ ገዢዎች የምንባለው የሰራንላቸው የኮሎኒ ማፕ ለምን ይዘው ለድርድሩ አልተጠቀሙበትም? የ1964 የካይሮ ውሳኔም ተገንጣዩ የመጨረሻው ቅኝ ገዢ የሰጠው መሬት/ቅርጽ ይዞ ይሄዳል ይላል። መጨረሻ ቅኝ ብለው ወያኔዎች የሰየሙንም እኛ ከሆንን፤ ኢትዮጵያዊያን ቢሆኑ ኖሮ የኛን ካርታ ይዘው መከራከር ነበረባቸው። መልስ የሚያሻው ጥያቄ ነው።

ባንዳዎቹ በእውነተኛ ክርክር ጎሮራቸው ስለታነቁ ለዚህ ጥያቄ እስካሁን ድረስ መልስ ሲሰጡበት የሰማነው መልሳቸው “ኢትዮጵያ ያለ ወደብ 25 አመት ኖራለች ስለዚህ አያስፈልገንም” ወይንም ፤ በስብሐት ነጋ መልስ መሰረት “ዓሰብ ሳይሆን ጅቡቲ ነው ለኛ ለኢትዮጵያ የሚረባው” (ዓሰብን አትጠይቁ ወደ ትግራይ- ለትግራይ ትግርኛ መርሃ ግብሩ ስለሚጠቃለል ማለቱ ነው። ወያኔ “ዓሰብ” በትግራይ ክልል ያካተተ ካርታ ሰርቶ እንደነበረም ታውቃላችሁ።) የመሳሰሉ የማሃይሞችና ተረብተኞች መልስ ከመስጠት በቀር ለጥያቄአችን ቀጥተኛ መልስ ሊመለሱልን አልቻሉም። 25 አመት ያለወደብ ከጅቡቲ፤ከሶማሊ ወደብ እየተከራዩን ኑረናል፤ ስለዚህ ያለ ወደብ መኖር ይቻላል፤ የሚለው “መልስ ሲያጡ የሚመልሱት መልስ” የውዳቂዎች መልስ ነው። ለነገሩ ኑሮ አይባልም እንጂ ኤርትራም እኮ 25 አመት ወደቧ ባዶ ሆኖ ኖራለች። ጥያቄአችን አጭር፤ቀጥተኛና ግልጽ ነው!!! 25 አመት ዳከረው መልስ ያጡበት ጥያቄ አሁንም እንዲመልሱልን እንጠይቃቸዋለን።

ዛሬ የፈራነው እና የተነበይነው ተከሰተ እና ዓሰብ እና ምጽዋ ኢራኒያኖች እና ዓረቦች ይዘውታል።፡ይህንን ስንል፤ ውሽታሞች ሲሉን የነበሩት ዛሬ “ውሸታሞቹ” እኛ ወይንስ እነሱ? መልስ እንሻለን። ይህንን እንዳነበባችሁ ታስታውሳላችሁ?

(ሳውዝ ፍሮንት በመባል የሚታወቀው ‹‹ፎረይን ፖሊሲ ዲያሪ›› በሚባል ፕሮግራሙ የቀረበው አጭር ግን ጥልቅ መረጃ የያዘ ዘጋቢ ፊልም ነው፡፡ “Arab Coalition Expands into the Horn of Africa” በሚል ርዕስ ባሰራጨው ዘጋቢ ፊልም፣ ‹‹ይኼ ለኤርትራ ከፍተኛ የገንዘብ ምንጭ ብቻ ሳይሆን፣ እስካሁን የገጠማትን የመነጠል ችግር የሚፈታ ነው፤›› ብሎታል፡፡ በአፍሪካ ኅብረት የደረሰባትን ‹‹የሥርዓተ አልበኝነት›› ፍረጃም ነፃ ያወጣል ብሏል፡፡ ‹‹በእርግጥ ኤርትራ ማንም ቢሆን ገንዘብ የሚሰጣት ከሆነ ከመደገፍ ወደኋላ አትልም፤›› ይላል በዘጋቢ ፊልሙ ላይ የቀረበው ሐተታ፡፡ በአሰብ እየተገነባ ያለው ወታደራዊ ኃይል በአፍሪካ ቀንድ ከዚህ በፊት ያልነበረና የመጀመሪያው መሆኑንም ጠቅሷል፡፡ ‹‹ለአካባቢው (ለአፍሪካ ቀንድ) አደገኛ እንቅስቃሴ›› በማለት የአፍሪካ ቀንድ የዓለም አቀፉ የግጭት እንቅስቃሴ መናኸሪያ ሊሆን እንደሚችል ግምቱን ያስቀምጣል፡፡”

ይህ ሃቅ ዛሬ እውን ሆኖ ከተገኘ በኋላ ያለ ወደብ መኖር ይቻላል ሲሉን የነበሩ የወያኔ አለቅላቂ አሽከሮች (አይጋ ድረገፆች፤ ትግራይ ኦን ላይን እና የወያኔ ሎሌዎች ሁሉ) ዛሬ ዓረቦች ዓሰብን ተቆጣጥረውታል ሲባል “ መንግሥታችን፤ እባካችሁ ወሳኝ የሆነ እርምጃ በመውሰድ ኢሳያስን አስወግዳችሁ ስጋት የሆኑብንን ዓረቦችን ኣባርሩልን” ብለው ሲጮሁ ሰምተናል። ውሸታሞቹ እኛ ወይስ እነሱ? ነገ እስላመዊ ወንድማማችነትና እና ዓረባዊ ሕብርት ይዟቸው “ሶማሊም ፤ጅቡቲም” ወደቦቻቸውን ቢከለክሉን እና ኤርትራ /ግብፅ'ሳወዲ ኢራን ጋር ጦርነት ብንገጥም....... መሳሪያ በየት ይገባል፤ ምግብስ በየት ይወጣል፤ ሸቀጡስ በየት ይወጣል ይገባል? ይሆናል ያልነውን ሁሉ እየሆነ ነው እና መልስ ስጡን እንጂ! )

